የሠ/መ/ቁጥር 244430

ሀምሌ 26 ቀን 2016ዓ/ም

**ዳኞች ፡- ብርሃኑ አመነው**

**በዕዉቀት በላይ**

**ቀነዓ ቂጣታ**

**ብርሃኑ መንግሥቱ**

**ማርታ ተካ**

**አመልካች፡-** አቶ ጃቢር ሼክ ኢብራሂም

**ተጠሪዎች** ፡- 1. አቶ ሀሰን ሼክ አደን አህመድ

2. አቶ መሀዲ ሼክ አደም

3. የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ግብርና እና የገጠር ልማት ቢሮ

4. የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማት እና ማኔጅመንት ቢሮ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የክርክር አመራር የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች በተጠሪዎች ላይ በመሰረቱት ክስ ፡- የቦታውን አዋሳኝ በመጥቀስ በግምት ከ3-4 ሄክታር የሚሆን የእርሻ መሬት ከንጉሱ ዘመን ጀምሮ በወላጆቹ የፀና ባለመብትነት ሲተዳደር የነበረውን ወራሽነቴን አሳውጄ ውርሱ ተጣርቶ መሬቱ የወላጆቼ መሆኑ ተረጋግጦ ውሳኔ አግኝቷል፡፡አባቴ ለ1ኛ እና 2ተኛ ተጠሪዎች አባት ልጆቹ አካለ መጠን እስኪደርሱ መሬቱን እያረሰ እንዲጠቀም እና ከምርቱ የተወሰነ እንዲያካፍለው ሰጥቶት አባታችን የሞተ በመሆኑ መሬቱ የተጠሪዎች አባት እጅ ሊቆይና አባታቸውም ሲሞት በእጃቸው ሊቆይ ችሏል፡፡3ኛ ተጠሪ ያለ ምንም ሕጋዊ መሰረት ለ1ኛ ተጠሪ የገጠር መሬት የይዞታ ማረጋገጫ ሰርቶ የሰጠ ሲሆን 4ኛ ተጠሪ በተመሳሳይ ይዞታ ላይ ያለምንም ሕጋዊ መሰረት ለ1ኛ ተጠሪ የከተማ ቦታ የይዞታ ማረጋገጭ በሊዝ ስሪት በከፊል ይዞታው ላይ መስጠቱ ሕገ-ወጥ ድርጊት ነው፡፡ ስለሆነም 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ያለምንም የሕግ መሰረት ለ1ኛ ተጠሪ የሰጡት የገጠር እና የከተማ የመሬት የይዞታ ማረጋጫ እንዲሰረዝ እና 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ይዞታውን ለቀው እንዲያስረክቡ እንዲሁም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርዮ አረጸደ ምዓለማአ የገ ለግልም!

ከእርሻው መሬት የታጣውን ጥቅም መሬቱ ከተለቀቀ በኋላ ክስ አቅርበን እንድናስወስን መብቴ እንዲጠበቅልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስ:-አመልካች የመፋለም ክስ ለማቅረብ መብት እና ጥቅም የለውም፡፡ የመሬቱ ባለሀብት ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡አመልካች ይዞታው በተደረገው የውርስ ማጣራት መሰረት የአባቴ ነው የሚል ሲሆን ይህ ከሆነ ደግሞ ሊያቀርብ የሚችለው ክስ ወራሽ ሳይሆኑ የያዙትን የውርስ ሀብት ለቀው ያስረክቡ በሚል እንጂ የመፋለም ክስ ማቅረብ አይችልም፡፡ከዚህ አንፃር የቀረበ ክስ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑ በይርጋ የሚታገድ ነው፡፡መያዝ የሚገባውን ፍሬ ነገር አሟልቶ ያልያዘ እና ይዞታው ለአባታችን መቼ እንደተሰጠው ያልገለፀ በመሆኑ የመከላከል መብታችንን የሚያሳጣ ነው፡፡በዚሁ ፍርድ በመ/ቁት 82092 ላይ ያቀረቡት ክስ እየታየ እያለ ያቀረቡት ክስ ስለሆነ ዉድቅ ሊሆን ይገባል የሚሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን እና ፍሬ ነገሩን የሚመለከት መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡ 4ኛ ተጠሪ ባቀረበዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በሰ/መ/ቁጥር 17712፣27604 እና በሌሎች መዛግብት ላይ በተሰጠዉ የሕግ ትርጉም መሰረት አመልካች ካርታ ይሰረዝልኝ በማለት በቀጥታ ክስ ለማቅረብ መብት የለውም፡፡ ፍርድ ቤቱም ይህን ጉዳይ አይቶ የመወሰን ስልጣን የለውም፡፡አመልካች በአንድ በኩል ካርታ ይሠረዝልኝ በሌላ በኩል ካርታ የተሰጠበት አግባብ ይመርመርልኝ እያለ በሁለት የተለያዩ አካላት የሚታዩ ምክንያቶች ላይ ማቅረብ የማይገባዉ ከመሆኑም በተጨማሪ አመልካች መብትና ጥቅሙን አረጋግጦ ስላልቀረበ ክሱ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 87963 ላይ በቀን 23/03/2015ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ:-አመልካች በክሱ ላይ ሟች በሞተ እና ዉርሱ በተከፈተ ጊዜ ሟች ቀድሞዉኑ ከ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች አባት ጋር ባደረገዉ ስምምነት መሰረት ክርክር የተነሳበት እና የሟች ዉርስ ሃብት መሆኑን የገለጸዉ የእርሻ ይዞታ በተጠሪዎች እጅ የነበረ መሆኑን ግልጿል፡፡ክርክር የተነሳበት እና የሟቹ ውርስ ሀብት መሆኑ የተገለፀው የእርሻ ይዞታ በ1ኛ እና 2ተኛ ተጠሪዎች እጅ የነበረ ከመሆኑ አንፃር አመልካች እንደ አንድ ወራሽ በዚሁ ላይ ያለውን የውርስ መብት በውርስ ደንብ መሰረት ሊሰራበት ከሚገባው በቀር የውርስ ሀብት የመፅደቅ ውሳኔ መስጠቱ በውርስ ደንብ መሰረት ሊሠራበት ከሚገባዉ በቀር የዉርስ ሀብት ሪፖርት የመጽደቅ ዉሳኔ መሠጠቱ በዉርስ ደንብ ሊመራ የሚገባውን ጉዳይ በጠቅላላው የንብረት ሕግ ማዕቀፍ ስር በተመለከቱ ድንጋጌዎች መነሻነት በንብረት ላይ የፀና የባለቤትነት መብት ያለውና ይህንን ያረጋገጠ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብት በባለቤትነት መንፈስ እያስተዳደረ ያለው የማይንቀሳቀስ ንብረቱ በመነጠቁ ወይም እንዳይለገል በመደረጉ የሚያቀርበውን የመፋለም ክስ ለማቅረብ መብት እና ጥቅም የሚያጎናፅፍ አይደለም፡፡አመልካች በክሱ እንዳቀረበው ክርክር የተነሳበት ይዞታ የይዞታው ባለሀብት እና አውራሹ ባደረገው ስምምነት መሰረት ለተጠሪዎች አባት እንዲጠቀምበት የሰጠው ከመሆኑ ባለፈ የአመልካች አውራሽ ሞትን ተከትሎ ይዞታው በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እጅ መሆኑ ቀጥሎ ባለበት ሁኔታ ይዞታውን ለመረከብ የሚቀርብ ክስ በውርስ ደንብ መሰረት የሚመራ እና በዚሁ አግባብ ዳኝነት ሊሰጥ ከሚችል በቀር በጠቅላላ የንብረት ሕግ ማዕቀፍ አንፃር የጠየቀው ዳኝነት ሊሰጥ የማይችል በመሆኑ በቀጥታ የመፋለም ክስ ለማቅረብ አመልካች መብት እና ጥቅም እንዲሁም የክስ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርዮአረጸደምዓለማአየገለግልም!

ምክንያት የለውም በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 33/2 እና 231 በመጥቀስ ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

አመልካችም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 20316 ላይ በቀን 17/06/2015ዓ.ም በሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 ተጠሪን ሳያስቀርብ ሰርዞባቸዋል፡፡

አመልካች በቀን 15/07/2015ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ አጭር ይዘት፡-አንድ ሰው በሌላው ሰው ላይ ክስ ለማቅረብ የሚችለው ክስ ባቀረበበት ነገር ላይ ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ መብት ካለው ነው፡፡በአንድ ንብረት ላይ የባለሀብትነት መብት የሚመነጨው ወይም የሚተላለፈው ደግሞ ከሕግ እና ባለጉዳዮች ከሚያደርጉዋቸው ሕጋዊ ተግባራት መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1184 ስር ተመልክቷል፡፡ክስ የቀረበበት የእርሻ ይዞታ የአመልካች ወላጆች የነበረና ለ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች አባት እንዲጠቀምበት ከተሰጠው በኋላ መሬቱን ሳይመልስ በመሞቱ ተጠሪዎች እየተጠቀሙበት የሚገኙ ስለመሆኑና 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ከሕግ ውጭ በተመሳሳይ ይዞታ ላይ የከተማ እና የገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ በ1ኛ ተጠሪ ስም የሰጡ በመሆኑ ከሕግ ውጭ የተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰረዝና 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ይዞታውን ለቀው እንዲያስረክቡ ክስ ቀርቧል፡፡በመሰረቱ ለቀረበው ክስ እልባት ሊሰጥ የሚችለው በውርስ ሕግ ነው፤ በንብረት ሕግ ነው ወይስ እንደአግባብነቱ ሁለቱን በማጣመር ነው የሚለው ፍርድ ቤቱ ለሚሰጠው ፍርድ መሰረት ሊያደርገው የሚገባ እንጂ ከሳሽ የክሱን ምክንያት እና የሚጠይቀውን ዳኝነት ከማስቀመጥ ውጭ በውርስ ሕግ ወይም በንብረት ሕግ መሰረት ክስ አላቀረብክም ተብሎ ክሱን ለማቅረብ መብትና ጥቅም የለውም ሊባል የሚችልበት የሕግ መሰረት የለም፡፡በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 999 እና 1206 ተጣጥመው ሊተረጎሙ የሚችሉ እንጂ የሚቃረኑ አይደሉም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 999 መሰረት የውርስ ሀብቱ መብት በሌለው ሰው የተያዘበት ሕጋዊ ወራሽ ንብረቱን እንዴት ያገኛል ለሚለው እልባት የሚሰጥ ሲሆን፣የሚጠይቀው የመብት አድማስ ምን ይሆናል የሚለው ምላሽ የሚያገኘው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1184 እና 1206 እንዲሁም በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ መሠረት ነዉ፡፡

በተጨማሪም አንድ ለፍርድ ቤት የቀረበ ክስ የክስ ምክንያት አለው የለውም ብሎ ለመለየት ክሱ የቀረበበት ሕግ መጠቀስ ግድ አይደለም፡፡ እንደውም የክስ አቤቱታ በሚቀርብበት ጊዜ ለክሱ ምክንያት የሆነው ፍሬ ነገር እና የሚጠየቀው ዳኝነት እንጂ የሕግ ዝርዝር ትንታኔ ሊይዝ እንደማይገባው የአቤቱታ አቀራረብ ደንብ ያስረዳል፡፡አመልካች ክስ ባቀረብኩበት የገጠር መሬት ላይ ከውርስም ሆነ ከገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕጎች የመነጨ መብት ያለኝ ስለመሆኑ በመሬቱ ላይ የፀና የመጠቀም መብት የነበራቸው ሼክ ኢብራሂም ኤሊ ልጅና ወራሽ መሆኔን አረጋግጬ ውርስ አጣርቻለው፡፡ውርስ ባይጣራም በመብቴ ላይ ለውጥ አይፈጥርም፡፡መብቱ በሌላቸው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የተያዘው የገጠር መሬት ይለቀቅልኝ የሚለውም ሆነ ከሕግ ውጭ በይዞታው ላይ በ3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች የተሰጡት ሁለት የከተማና የገጠር መሬት ይዞታ

ማረጋገጫዎች እንዲሰረዙ የቀረበው የዳኝነት ጥያቄም በፍ/ቤት ታይቶ ዳኝነት ሊሰጥባቸው የሚችሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ሁለቱም የይዞታ ማረጋገጫዎች የተሰጡት የአስተዳደር ሥነ- ሥርዓት አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ነው፡፡በመሆኑም ክስ የቀረበበት መሬት የሼክ ኢብራሂም አሊ መሆኑ እና አመልካች ልጃቸው መሆኔ ከተረጋገጠ በውርስ ሕጉም ሆነ በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕጎች መሰረት በክሱ የጠየቀኩትን ዳኝነት ለማግኘት ሕግ ይፈቅድልኛል፡፡የቀረበው ክስ የክስ ምክንያት አለው የለውም ለማለት በማስረጃ ሊመዘን የሚገባው ጉዳይ ግምት ውስጥ ሊገባ አይገባውም፡፡የቀረበው ክስ በሕግና በማስረጃ ቢረጋገጥ መብቱን ያገኛል አያገኝም የሚለውን ጥያቄ ፍ/ቤቱ በማንሳት በአወንታ የሚመለስ ከሆነ ክሱ የክስ ምክንያት አለው የሚል ድምዳሜ ሊያዝበት እንደሚገባ መረዳት ይቻላል፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ክሱ የክስ ምክንያት የለዉም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ በሰ/መ/ቁጥር 135775 (በቅጽ 21) እና በሰ/መ/ቁጥር 150309 ላይ የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 231(1/ሀ) ስር የተደነገገዉን የሚቃረን እና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ተሽሮ ጉዳዩን ከስረ ነገሩ አይተዉ እንዲወስኑ ሊመለስላቸዉ ይገባል በማለት ጠይቀዋል፡፡

ችሎቱ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ በመመርመር የስር ፍርድ ቤት አመልካች ክስ በመሰረቱበት ጉዳይ ላይ በቀጥታ የመፋለም ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም የላቸዉም፤እንዲሁም ክሱ የክስ ምክንያት የለዉም በሚል ክሱን ዉድቅ ማድረጉ አግባብ መሆን አለመሆኑን በሰ/መ/ቁጥር 150309 ላይ ከተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንጻር እንዲመረመር ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ አዝዟል፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በቀን 29/04/2016ዓ.ም በጋራ በተፃፈ መልሳቸው - አመልካች በክሳቸዉ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ያለምንም የሕግ መሰረት በሕገ-ወጥ መንገድ የያዙትን የመሬት ይዞታ ለቀው እንዲያስረክቡ የቀረበ የመፋለም ክስ ነው ቢልም የክሱ ዝርዝር ይዘት ላይ መብቱን ለመጠየቅ መሰረት ያደረጉት የአባቴ የውርስ ሀብት መብት በሌላቸው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የተያዘብኝ ስለሆነ ይለቀቁልኝ የሚል ነው፡፡የውርስ ሀብት ተጣርቶ የሚሰጥ ማስረጃ ውርስ ሀብቱን የወራሽነት መብት ሳይኖራቸዉ ከያዘው ሰው ላይ በውርስ በሕጉ መሰረት የውርስ ሀብት ይለቀቅልኝ የሚል ክስ ማቅረብ ከሚችሉ በስተቀር የመፋለም ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም ስለሌላቸዉ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የመፋለም ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም የላቸዉም በማለት በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 150309 ላይ የሰጠዉ የሕግ ትርጉም ከተያዘዉ ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ጉዳይ ላይ የተሰጠ ባለመሆኑ ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት የለዉም፡፡መሬቱ የአመልካች አባት ይዞታ ነው አይደለም የሚለው ጉዳይ ፍርድ ቤት የሚያጣራው መሆኑ እንዳለ ሆኖ ይህ ክርክር ከመነሳቱ አመታት በፊት መሬቱ ወደ ከተማ ክልል የተካለለና የሊዝ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት ከፊል መሬቱ ለኢንቨስትመንት በሊዝ የተሰጠ መሬት ነው፡፡የአመልካች አባት ለተጠሪዎች አባት መሬቱን ከሰጡ ከ35 ዓመት በላይ የሆነው ሲሆን በመቀጠልም የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች አባት ከሞቱና ተጠሪዎች በዚህ መሬት መጠቀም ከጀመሩ 30 ዓመት የሚጠጋ ሲሆን የአመልካች አባት በመሬቱ የመጠቀም መብታቸውን ለረዥም ጊዜ የተውና ለሌላ ሰው አሳልፈው የሰጡ መሆኑ ሲታይ የአመልካች አባት ከጅምሩም በመሬቱ የመጠቀም የጸና መብት እንደሌላቸው ወይም ይህን መብት እንዳጡ ያሳያል፡፡እንዲሁም አመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይሰረዝልኝ በማለት የጠየቁት ዳኝነት በሰ/መ/ቁጥር

220042 ላይ በተሰጠዉ ትርጉም መሰረት በአስተዳደር ስነ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2013 መሰረት ሊታይ የሚገባዉ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የለዉም፡፡ ስለሆነም አመልካች ይህንን ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም እንዲሁም የክስ ምክንያት የላቸውም በማለት የተሰጠው ብይን እንዲጸናልን ብለዋል፡፡

4ኛ ተጠሪ በቀን 26/04/2016ዓ.ም በተጻፈ መልሱ አመልካች ያቀረበው ክስ የካርታ ይሰረዝለኝ ጥያቄን የሚመለከት በመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 17712 (ቅጽ 2) ፣57011 (ቅፅ 13)14554 (ቅፅ 6) እና በሌሎች መዛግብት ላይ በተሰጠዉ የሕግ ትርጉም መሠረት አስተዳደራዊ ዉሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን የለዉም፡፡እንዲሁም የጠየቁት ዳኝነት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይሰረዝልኝ በመሆኑ ይህ ደግሞ በአስተዳደር ስነ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2013 እና በሰ/መ/ቁጥር 220042 ላይ በተሰጠዉ የሕግ ትርጉም መሰረት የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በቀጥታ ክስ ተቀብሎ ለመዳኘት ሥልጣን የለዉም፡፡አመልካች በ4ኛ ተጠሪ ላይ የመፋለም ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም እንዲሁም የክስ ምክንያት የላቸውም፡፡ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ብይን የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

3ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት መልስ ባለማቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡አመልካች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ እንዲሁም ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያቀረቡትን ክርክር የሚመለከት ሲሆን እኛም አስቀድሞ የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ ጉዳዩን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደተመረመረዉም በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(1 እና 7) እና በሌሎች የንብረት ሕግጋት ላይ የተመለከተዉ ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰዉ በንብረት መብቱ ላይ ጥሰት እንዳይፈጠርበት በሕገ መንግስቱና በየተዋረዱ ባሉ ሕግጋት ጥበቃ ተደርጎለታል፡፡ይህ መብት ንብረቱን በዉርስ ወይም በሌላ መንገድ ማስተላለፍን ያካተተ ነዉ፡፡ የዚህ ጥበቃ አስፈላጊነትም ማንኛዉም ሰዉ ንብረቱን በሠላም እንዲጠቀምበት ወይም እንዲገለገልበት ለማስቻል እንዲሁም የንብረት መብት በመጠበቅ በንብረቱ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ማግኘት እንዲችል ነዉ፡፡አንድ ሰዉ አንድን የፍትሐ ብሔር ክስ ይዞ ወደ ፍርድ ቤት ወይም በሕግ ስልጣን ወደ ተሰጠዉ የዳኝነት አካል የሚሄደዉ ዳኝነት ፍለጋ ነዉ፡፡ ፍርድ ቤቶች ክርክሮችን በዘፈቀደ ሳይሆን በሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረት መምራት ይኖርባቸዋል፡፡ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ መሠረታዊ ዓላማ እና ግብ የፍትሐ ብሔር ክርክሮች ምክንያታዊ በሆነ በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ የሰዉና የቁስ ሀብት ታይተዉ ፍትሐዊ እልባት እንዲያገኙ ማድረግ ነዉ፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድ ፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጋችን የተለያዩ ደንቦችና መርሆዎችን ደንግጓል፡፡ በክርክር ሂደት እነዚህን ደንቦች እና መርሆዎች እንደየአግባብነታቸዉ ሥራ ላይ ማዋል የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት መብት ያገናዘበ፣ የተከራካሪ ወገኖች ብሎም የፍርድ ቤቱ ወጪ እና ጊዜ ያላግባብ እንዳይባክን በማድረግ ሥነ

ሥርዓታዊ ፍትሕን በማረጋገጥ በመጨረሻም በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ዉሳኔ እንዲሰጥ በማድረግ ረገድ የሚኖረዉ ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ዕዉቅና ከተሰጣቸዉ መርሆዎች እና ደንቦች ዉስጥ አንዱ አንድ የፍትሐ ብሔር ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠዉ አካል ሊቀርብ የሚችልበትን ቅድመ ሁኔታ የሚመለከት ደንብ ሲሆን፣ ይህም በሕጉ ቁጥር 32 እና ተከታዮቹ ላይ የተመለከተዉ ነዉ፡፡ ከዚህም ዉስጥ አንዱ ከሳሽ የመሆን ችሎታ በሚል ርዕስ በቁጥር 33 ላይ የተደነገገዉ ሲሆን ለተያዘዉ ጉዳይ አግባብነት ያለዉ በቁጥር 33(2 እና 3) ስር የተደነገገዉ ደንብ ነዉ፡፡

ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ በቁጥር 33/2 መሠረት ከሳሽ በሕግ አግባብ ሊወሰንለት የሚችል ከሕግ ወይም ከዉል የመነጨ መብት ያለዉ መሆኑን በክሱ እንዲያሳይ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ከሳሽ ክሱን በሚያቀርብበት ጊዜ ለክሱ ወይም ለጠየቀዉ ዳኝነት ምክንያት ናቸዉ የሚላቸዉን ፍሬ ነገሮች በዝርዝር የመግለጽ ግዴታ ያለበት ሲሆን፣ ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የቀረበዉን ክስ የሚቀበለዉ ክርክሩ ቢቀጥል በከሳሽ ጥያቄ መሠረት ሊወሰን የሚችል ከሕግ ወይም ከዉል የመነጨ መብት ስለመኖሩ የከሳሽ ክስ ይዘት የሚያሳይ መሆኑን በቅድሚያ ሲያረጋግጥ ነዉ፡፡ ከሳሽ የሚያቀርበዉ ክስ ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮችና የተፈጠሩበትን ጊዜና ስፍራ እንዲሁም ተከሳሹ ለክሱ ተጠሪ ወይም ኃላፊ የሚሆንበትን ምክንያት ሊይዝ እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ቁጥር 33/3 እና 222 (1/ሸ እና ረ) ላይ በአስገዳጅ መልክ ተደንግጓል፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 136775 ፣182161 እና 216139 ላይ በተሰጠዉ ዉሳኔ አንድ በፍርድ ቤት የቀረበ ጉዳይ የክስ ምክንያት አለዉ ብሎ ለመወሰን የሚቻለዉ በክሱ ላይ የተገለጸዉ ነገር ቢረጋገጥ ከሳሹ የጠየቀዉን ዳኝነት ለማግኘት ሕግ ይፈቅድለታል ወይ የሚለዉ ጥያቄ ሲነሳ ፍርድ ቤቱ አዎንታዊ ምላሽ ለመስጠት የሚችል የሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ አመልካች በፍሬ ነገር ደረጃ የአመልካች አባት የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች አባት መሬቱን እያረሱ ከምርቱ ለአባታቸዉ እያካፈሉ እንዲጠቀሙ እንደሰጧቸዉ፤የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች አባት በዚህ መልኩ እየተጠቀሙ ቆይተዉ እንደሞቱና ከዚህ በኋላ መሬቱ ወደ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እጅ እንደገባ ፤እንዲሁም መሬቱ በዉርስ ሊተላለፍላቸዉ የሚገባ መሆኑን በክስ ማመልከቻዉ ላይ አስፈረዋል፡፡አመልካች በዚህ መልኩ በክስ ማመልከቻቸዉ ላይ ያሰፈሩት ፍሬ ነገር በእርግጥ ያለና ትክክል መሆኑ በተገቢዉ የክርክር ደረጃ ላይ በማስረጃ የሚረጋገጥ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች ክስ በተመሰረተበት መሬት ላይ መብት እንዳላቸዉ ማሳየታቸዉን ወይም ማረጋገጣቸዉን የሚያሳይ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 33/2 ስር ሕጉ የሚጠይቀዉን መስፈርት የሚያሟላ ነዉ፡፡ ክስ በተመሰረተበት ነገር ወይም ሀብት ላይ አለኝ ብሎ የሚያምነዉን ከሕግ ወይም ከዉል የመነጨ መብት ወይም ጥቅም እንዲሁም የክሱን ስረ ነገርና የክሱን ምክንያት በክስ ማመልከቻዉ ላይ የመግለጽ መብት የከሳሽ ነዉ፡፡ በክሱ ከሳሽ አለኝ ብሎ የገለጸዉ መብት ወይም ጥቅም የሚገዛበትን ተገቢዉን ሕግ ለይቶ ተፈጻሚ ማድረግ ደግሞ የፍርድ ቤት ኃላፊነት ነዉ፡፡ በመሆኑም የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እጅ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርዮአረጸጸምዓለማአየገለግልም!

መሆኑ ቀጥሎ ባለበት ሁኔታ ይዞታውን ለመረከብ ክስ ለማቅረብ የሚችለዉ በውርስ ደንብ መሰረት እንጂ በጠቅላላ የንብረት ሕግ ማዕቀፍ አንፃር በቀጥታ የመፋለም ክስ የማቅረብ መብት የላቸዉም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 33/2 የተደነገገዉን ያልተከተለ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

በተጨማሪም አመልካች በክስ ማመልከቻቸዉ ላይ በዉርስ ሊተላለፍላቸዉ የሚገባዉን በክሱ የተጠቀሰዉን መሬት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች መብት ሳይኖራቸዉ እንደያዙና በከፊል 1ኛ ተጠሪ በስማቸዉ እንዳስመዘገቡ፤ እንዲሁም 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች መብት ለሌላቸዉ ለ1ኛ ተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መስጠታቸዉ ገልጸዋል፡፡ይህም አመልካች ተጠሪዎችን የከሰሱበትን ምክንያት በክስ ማመልከቻቸዉ ላይ መግለጻቸዉን የሚያሳይ ነዉ፡፡ከላይ በተጠቀሰዉ ሰ/መ/ቁጥር 136775 ላይ በተሰጠዉ የሕግ ትርጉም ላይ እንደተመለከተዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች መብት ሳይኖራቸዉ ይዘዉ በ1ኛ ተጠሪ ስም ማስመዝገባቸዉ እና 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎችም መብት ለሌላቸዉ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መስጠታቸዉ አግባብነት ባለዉ ሕግና ማስረጃ ከተረጋገጠ በአመልካች ክስ መሰረት ሊወሰን ይችላል፡፡በመሆኑም አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 33/3 መሠረት ተጠሪዎችን የሚያስከስስ የክስ ምክንያት ገልጸዉ ያቀረቡት ክስ ሆኖ እያለ ክሱ የክስ ምክንያት የለዉም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ ሥነ ሥርዓታዊ ካለመሆኑም በተጨማሪ በተጠቀሱት መዛግብት ላይ ይህ ችሎት የሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሸ) እና 10(1/ሀ) መሰረት ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አመልካች በክሱ ዳኝነት የጠየቁ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ለ1ኛ ተጠሪ የሰጡት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰረዝ ብቻ ሳይሆን ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የመሬት ይዞታ በዉርስ ሊተላለፍላቸዉ የሚገባ ይዞታ እንደሆነ እና 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች መብት ሳይኖራቸዉ መሬቱን ይዘዉ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ማዉጣታቸዉ ተረጋግጦ እንዲወሰን ጭምር ነዉ፡፡ከዚህም በተጨማሪ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የአስተዳደር አካላት ሳይሆኑ በአከራካሪዉ ይዞታ ላይ የይዞታነት መብት አለን በሚል የሚከራከሩ ናቸዉ፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 220582 ላይ ካርታ እንዲመክን የቀረበው ክስ በዳኝነት ክለሳ የሚታይ ነው በማለት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሠረት ተደርጎ የተወሰነ ከመሆኑ ባሻገር የመጨረሻ ዳኝነቱ ተመሳሳይ የሆነ ነገር ግን እንደ ክስ አቀራረብና ይዘት የሚነሳው ጭብጥ የተለያየ በሆነ ጊዜ ሁሉም ክስ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሠረት ብቻ እንዲታይ አስገዳጅ ሆኖ የተሰጠ ትርጉም እንዳልሆነና የቀረበዉ ክስ ይዞታው የማን ነው የሚል ጭብጥ የሚያስነሳ በሆነ ጊዜ በዳኝነት ክለሳ ሥርዓት ላይ ንብረቱ የከሳሽ ነዉ ወይስ የተከሳሽ የሚል የንብረት ክርክር ጭብጥ ተይዞ ሊወስና ስለማይችል እንዲህ አይነት ክርክር ሲያጋጥም በቀጥታ ክስ ሊታይ እንደሚችል ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 229531 እና 232118 ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በተያዘዉም ጉዳይ ተመሳሳይ የክርክር ጭብጥ ያለበት በመሆኑ አመልካች በተጠሪዎች ላይ የመሰረቱት ክስ በክለሳ ሳይሆን በቀጥታ ክስ ለፌዴራል

መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመቅረቡ የተፈጸመ ስህተት ባለመኖሩ ተጠሪዎች ከዚህ አኳያ ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልንም፡፡በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 87963 ላይ በቀን 23/03/2015ዓ/ም የሠጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 20316 ላይ በቀን 17/06/2015 ዓ/ም የሠጠዉ ትዕዛዝ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዘጋዉን መዝገብ አንቀሳቅሶ የግራ ቀኙን ቀሪ ክርክር መርምሮ ሕግን መሠረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/2 መሰረት ተመልሶለታል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ ሲጠይቁ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
- በዚህ ችሎት ነሐሴ 25 ቀን 2015 ዓ/ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
- ዉሳኔዉ በቀን 09/11/2016 ዓ/ም ተነበበ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ ለፍርዮአፈጻጸምዓለማአየገለግልም!